በአማርኛ እና በግዕዝ ፊደል ገበታ ውስጥ የተደጋገሙ / በድምጽ የሚመሳሰሉ ፊደላት አሉ። ስለ እነዚህ ፊደላት አብዛኛው ሕብረተሰብ እምብዛም እውቀት የለውም፤ ከምሁራኑም የተለያዩ መላ መቶችና ምክንያቶች ሲሰጡ ታዝበናል። ይህን ግርግር ዶ/ር ለይኩን ብርሃን "የግዕዝ መማርያ" በሚለው መጽሐፋቸው እንደሚከተለው አስፍረውታል።

> "እነዚህ ፊደላት በማንነታቸው ጠብቆና ጠንቅቆ ባለመጻፍ ያስከተለው ችግር እጅግ ከፍተኛ ነው። ማንነታቸውን ማሳጣት ሀብት ንብረታቸውን መዝረፍ ሕጋዊና ተፈጥሮአዊ መብታቸውንና ማንነታቸውን የማጥፋት ወንጀል እየተፈፀመባቸው ነው። ለማን አቤት እንደሚባል ግን ችግር ሆኗል። 'ኩሎ ዐለው ውኅቡረ ዓለዉ።' ሁሉም ወንጀል ለመፈፀም አንድ ሆኑ ተባበሩ እንዳለው ዛሬ ፊደሎቻችን በቤተክርስቲያንም ሆነ ከዚያ ውጭ ባሉት ምሁራን የማንነት መብታቸውን በጋራ ጥሰው የሙት እርሻ ሆነው ተንከባካቢ አጥተው ዳዋውና ጠለንጁ ውጧቸው ይገኛሉ። ማንም እንደፈለገውና እንዳፈነነው የሚጽፋቸውና የሚያነባቸው ሆነዋል።"

ዶ/ር ለይኩን ይህን አቤቱታ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ፣ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌና አለቃ አሥረስ የኔሰው ጠቅሰው ቢያቀርቡም ትክክለኝውን መንገድና ሕግጋታቸውን ሳይጠቅሱ አልፈዋል። እኛም እንደፈተና እንዲሆን ይህን ርዕስ መርጠነዋል።

ከታች የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች እንደ መንደርደሪያ ይዛችሁ ስለነዚህ ፊደላት በሚከተለው መስፈርት መሰረት በጥናት የተጠናከረ ጽሁፍ ያቅርቡ።

መንደርደሪያ ጥያቄዎች

1. በአማርኛ ወይም በግዕዝ ፊደል ገበታ ላይ የተደጋገሙ ወይም በድምጻቸው አንድ የሆኑ ፊደላት ይዘርዝሩ?
2. አማርኛ ወይም በግዕዝ ፊደል ገበታ ላይ ፊደላቶቹ ለምን ተደጋገሙ?
3. ድግምግሞሾቹ የመጡት በመጀመርያ ፊደላቶቹ ሲቀረጹ ነው ወይስ በሂደት እየተጨመሩ ነው የመጡት?
4. የተደጋገሙት ፊደላት ለአማርኛ ሰዋሰው ጥቅማቸው ምንድን ነው? ከምን አንጻር ነው?
5. ለምን የተወሰኑ ፊደላት ብቻ ተድጋገሙ?
6. የተደጋገሙት ፊደላት የስማቸው መነሻው ምንድነው? ለምሳሌ:
    - ሀሌታ፣ ሐመሩ፣ ወዘተ...
7. በ ሀ፣ሐ፣ኀ፣አ፣ዐ የፊደል ተርታ ውስጥ የግዕዙ ፊደል እና የራብዕ ፊደል ተመሳሳይ ድምጽ አላቸው።
    - በርግጥም ድምጻቸው ተመሳሳይ ነውን?
    - የተለያየ ህግ እና አጠቃቀም አላቸውን?
8. በትግረኛ እና በግዕዝ ጽሁፎች ላይ በአብዛኛው የራብዕ ፊደላት ይታያሉ። ይህ ምክንያቱ ምንድን ነው?
9. በአጠቃላይ ተደጋግመው ወይንም ድምጻቸው የሚመሳሰሉ ፊደላት የአጠቃቀም ህግጋት አላቸው ውይ?

* ከዚህ ርዕስ ዙሪያ ተጨማሪ ጥያቄውች መጠየቅና መልስ ማዘጋጀት የበለጠ ነጥብ ያሰጣል።

መስፈርት

- ስለ ተሰጠው ርዕስ ምርምር/ጥናት ማካሄድ እና እውነትን የያዙ ግብአቶችን ማጠናከር፤
    - በርዕሱ ዙሪያ እውቀት ያላቸውን ሰዎች ፈልጎ ማነጋገር

    - ከመጻሐፍት እና ከድረ-ገጾች ማመሳከር/ማጣቀስ
- የተሰበሰበውን መረጃ ከ400 ባላነሰ ከ1000 ባልበለጠ ቃላት ተጠቅሞ በቀላሉ፣ ቅደም ተከተልን በጠበቀ እና ውበት ባለው መልኩ ተንትኖ እና አደራጅቶ በጽሑፍ ማቅረብ።
- የተጠቀሙትን ግብአቶች በስረአቱ footnote እና reference section ተጠቅመው ማጣቀስ።
- የተጻፈውን ጽሑፍ እና ግብአቶች ለምሳሌ፡ ቪድዮዎች፣ ምስሎች(ፎቶዎች፣ ስእሎች)፣ ድምፅ ቅጆዎች፣ የመፅሐፍ ገጽ ኮፒዎች ፣ ወዘተ... ግልጽ በሆነ መልኩ ሰይመው/label አድርገው በzip folder ከተው ኢሜል ማድረግ።

ግዴታ ያልሆነ ቢኖር ግን የሚመረጥ

- ጽሑፎች በጻሐፊው አንደበት ሲነበቡ አብዛኛውን ጊዜ ትክክለኛ ውበታቸው ይታያልና የጽሑፉን ውበት ወይንም መልእክት የበለጠ ያጠነክራል ብለው ካሰቡ የጻፉትን ጽሁፍ የድምጽ ቅጂ አያይዘው ይላኩልን። ጽሑፎን ሲያነቡ ፀጥታ የሰፈነበት ቦታ ይምረጡ።